# ዳግማዊ ምኒልክ / Emperor Menelik II of Ethiopia

leaimero.com/2013/12/05/4441/emperor-menelik-ii-of-ethiopia/



ም ኒ ል ክ

ጀግንነትና የአዋቂ ሰው ሥራ ታሪክ

የዘመናዊ ፖለቲካ አሠራር አጀማማር በኢትዮጵያ

*

ዜናው ተናፍሶ ወሬው ዓለምን አዳርሶ ጥቁሩንም ነጩንም ቀዩንም ፍጡር ከዚያም ራቅ ብለው የሚኖሩትንም ቢጫውንም ሕዝብ ያኔ ከነበሩት ከእነጌቶቻቸው ያስደነገጠው አንድ ነገር ቢኖር አደዋ ነው።

ትንሽ ቆይቶም ዜናው በቅኝ ግዛት መዳፍ ሥር ነጻነታቸውን ተገፈው የሚኖሩትን ያኔ „ባሪያዎች" ተብለው የተናቁትን ሕዝቦች የልብ ልብ ሰጥቶ ለመጀመሪያ ጊዜ ያስደሰተው በሁዋላም እንደምናነበው የታሪክ ጸሓፊዎችንም በብዙ ቦታ በጣም ያስገረመው የአደዋ ጦርነት፣ የተጀመረው በየካቲት

23 የቅዱስ ጊዮርጊስ ቀን 1888 ዓ.ም. ከጠዋቱ በኢትዮጵያ ሰዓት አቆጣጠር በአሥራ አንድ ሰዓት ላይ ነው። በዚህ በትክክል በስንት ሰዓት በሚለው ጥያቄ ላይ የተለያዩ ግምቶችና ማስረጃዎች -ከተለያዩ ሰዎች ይቀርባሉ።

በአንድ በኩል …ጦርና ጋሻ አንካሴና ጎራዴ፣ውጅግራ ጠበንጃና ምንሽር የያዙ ብሎኮና ነጠላ በርኖስና ካባ የደረቡ በባዶ እግራቸው የሚሄዱ ሰዎች ተሰልፈዋል። በሌላ በኩል …ይህን ያህል ሺህ ወታደሮች መድፍና መትረየስ ቦንብና ዘመናዊ ጠበንጃ ሽጉጥና ሴንጢ ይዘው ታጥቀው በጥይት ሊቆሉአቸው መለዮ ኮፊያቸውን አድርገው ተደርድረው መሽገው ቆመዋል ።



አውላላ ሜዳ ላይ ሁለቱ ጦሮች ቢጋጠሙ አሸናፊው ማን እንደሚሆን ለማንም ሰው ግልጽ ነው።ይህንኑ ተማምነው ነው ጣሊያኖች አገር አቋርጠው ባህር ተሻግረው ድንበር ጥሰው አድዋ ድረስ ዘልቀው ገብተው እዚያ አንደኛው ኮረብታ ላይ ለቀናት ለወራት የመሸጉት።

ገና በጥዋቱ ጦርነቱ ከመጀመሩ ጥቂት ደቂቃ በፊት አንድ መሥፍን የጦር ልብሱን እንደለበሰ አረፋ ከሚያደቅፈው ከነጩ ፈረሱ ላይ ዘሎ ወርዶ በጥድፊያና በኩራት እርምጃ የቤተክርስቲያኑን በር በርግዶ ሁለት እና ሦስት ጊዜ ዝቅ ብሎ ከተሳለመና ከአከተበ በሁዋላ በአራት ቢበዛ በአምስት ጋሻ ጃግሬዎቹ ታጅቦ ቀጥ ብሎ በቀጥታ ንጉሱ ወደ ተቀመጡበት ወንበር ዘልቆ ይራመዳል።

በዚያች ደቂቃ አጼ ምኒልክ ከሌሎቹ የተወሰኑ መኳንንቶቻቸውና መሣፍንቶቻቸው ጋር አንድ ላይ ሁነው አስቀድሰው ሥጋ ወደሙ ተቀብለው በሕልና ጸሎት አምላካቸውን ለመጨረሻ ጊዜ የሚማጸኑበት ደቂቃ ላይ ነበሩ።

ያ ኑብር መስሎ ዘሎ ከእነ ክብር ልብሱ መቅደሱ ድረስ -ጫማውን ያውልቅ አያውልቅ ምንም ይምናውቀው ነገር የለም- ግንባሩን ቋጥሮ መሬቱን እየረገጠ እያንቀጠቀጠ የገባው መሥፍን ጠጋ ብሎ ቀስ ብሎ በጆሮቸው ጦርነት መከፈቱን ያበስርላቸዋል።

„መ… ምን ዓይነት ጥሩ ወሬ ይዘህ መጣህ!“ ብለው ንጉሡ ፈገግ ይሉና ግድግዳው ላይ የተሳለውን በዓይናቸው የማሪያምን ሥዕል ፈልገው (ማሪያምን ከሁሉም አብልጠው ይወዳሉ ይባላል) ለሰከንድን ያህል ትክ ብለው ተመልክተው „እንግዲያውስ አሁኑኑ እንነሳ…“ ብለው ለእልፍኝ አስከልካያቸው ትዕዛዝ ይሰጣሉ። ያ መሥፍን ይህን ዜና ይዞ የመጣው ዲፕሎማቱም ጦረኛውም ራስ

መኮንን ነበሩ።




“…በቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን የኢጥዮጵያ መኳንንት ከመንጋቱ በፊት ተሰብስበው ቅዳሴ ይሰማሉ።የቤተክርስቲያኑ በር ክፍት ነው።ጳጳሱ አቡነ ማቴዎስ ቅዳሴውን በሚመሩበት ጊዜ ሁለት ጥየት ተተኮሰ።ይህም ምልክት ነበር። በዚህ ጊዜ የሐረርጌው ራስ መኮንን የንጉሡ ታማኝ አጎት ከቤተክርስቲያኑ ወጡ ።ከጥቂት ደቂቃዎች በሁዋላ ተመልሰው ገብተው የጣሊያኖንችን መምጣት ተናገሩ። ንጉሡም ወሬውን በጸጥታ አዳመጡ። ከዚያም ራስ መኮንን ወደ አቡኔ ዘንድ ቀርበው በሹክሹክታ ነገሩዋቸውና ተመልሰው ከመቀመጫቸው ተቀመጡ።እኡኡም መሰወቀላቸውን በቀኝ እጃቸው ይዘው በደከመ አነጋገር `ልጆቹ ዛሬ የእግዚአብሔር ፍረeድ የሚገለጽበት ቀን ነው።ሂዱ።ለሃይማኖታችሁና ለንጉሣችሁ ተከላከሉ።ሁላችሁንም ከኃጢአታችሁ እግዚአብሔር ይፍታህ´አሉ።መኳንንቱም አeየቀረበ መስቀል እየተሳለመ ወደ የሠፈሩ ሄደ….” ብሎ አንቶኒ ሞክለር ሁኔታውን ዘግቦአል።

ሁለት እርምጃ ከመኳንንቶች ጋር እንደ ተራመዱ አንዱ መሥፍን ከቦታው ሳይንቀሳቀስ ወደ ሁዋላ ቀርቶባቸው ኑሮ፣ ዞር ብለው ንጉሡ ተጵሮ እንደተነበበው „…ጸሎታችንን ለአምላክችን በበቂ አድርሰናል የሚቀረን አሁን የድርጊት ሥራ ነው። ይህ ደግሞ እዚያው የጦር ሜዳ ይለይልናል፣በል ተነስ…“ ብለው የቀሱን መስቀል ተሳልመው ወደፊት በችኮላ ተራምደው የሚቁነጠነጠው ፈረሳቸው ላይ ወጥተው ወደ ጦር ሰፈራቸው አፈሩንና አቧራውን ከአጀቦዎቻቸው ጋር ወደ ላይ እየመቱ የሚሆነው አይታወቅም ሁሉም ይከንፋሉ ።

ጎህ ሲቀደ በጥዋቱ እራስ መኮንን ከድንኳናቸው ወጥተው የጦር ልብሳቸውን ዕጣ ዕድሉ ለጠላት ከአመዘነ የመጨረሻ ቀናቸው ነውና፣ ገና ሳይለብሱ (እሳቸው ብቻ አይደሉም) ሌሎቹም በመነጽራቸው ተቻኩለው የእራሳቸውንም የጠላት መንደርን እሳቸው እንደቃኙት ሁሉ የጣሊያን ጀኔራሎች ራቅ ከአለው በትይዩ ከሚታየው ጋራ ጫፍ ላይ ሁነው ምኒልክ ከእነ አጃቢዎቻቸው አቧራውን እየመቱ ሲመጡ በቀዩ ጃንጥላቸው በአንዴ ለይተው አይተዋቸው ነበር። ቀይ የለበሰ፣ የአንበሳ ጎፈር እናቱ ላይ የጫነ ፣የክብር ልብሱን ያወጣ-የመጨረሻ ሰዓት ሊሆን ይችላል- ብዙ ነው።


ያቺ ቀይ የንጉሥ ጃንጥላ ግን እንደ ደረጃው መሣፍንቱና መኳንንቱ አረንጓዴና ጥቁር መያዝ ይችላል- በሁዋላም አጼ ኃይለ ሥላሴን ማይጨው ላይ ጉድ ልታደርግ ምንም አልቀረም ነበር።



በእሳቸው ላይ ተነጣጥሮ የተተኮሰው ጥይት እሳቸውን ስቶ የጃንጥላ ያዣቸውን ሕይወት ይዞ ሄዶአል።

ድብልቅልቁ መንደራቸው ንጉሡ እንደደረሱ ወጥቶ ጠብቆአቸዋል። አንዱ ጠበንጃውን ይዞ ጋሻና ጦር የያዘውን አለቃውን ተከትሎ አብሮ ወደ ገላጣው ሜዳ ይሮጣል።ሴቶች ከውድ ባሎቻቸው ይሰናበታሉ።

የደረሱ ልጆች ወዲያና ወዲህ ከአባቶቻቸው ወይም ከተላላቅ ወንድሞቻቸው ትዕዛዝ ለመቀበል ወዲያና ወዲህ ይነሰነሳሉ።ገና ያልተጫኑት ...በቅሎው አህያው ፈረሱ የቀንድ ከብቱ በጉና ፍየሉ ተደናግጠው በረቱ ውስጥ ይራወጣሉ።


Le Négus Ménélik à la bataille d'Adoua

ቀደም ሲል በጥዋቱ የመጀመሪያው ጥይት ድምጽ ሳይሰማ ብዙዎቹ የንጉሠ ነገሥቱን አጀብና ግርግር አይተው -እሳቸው ያኔ ለማስቀደስ ወደቤተክርስቲያን መሄዳቸው ነበር -ገላጣውን ደማቁን የጸሓዩዋን ጮራ፣ጎሁን አይተው „...ዛሬ ድሉ“ ሁሌ እንደሚሉትና እንደሚመኙት „የእኛ ነው...“ ብለው ቀኑን መርቀው ተቀብለው ነበር።

እንደዚህ ብለው ለማሰብም ወታደሮቹ ምክንያት ነበራቸው። ሁለት ሦስት ጊዜ በኃይለኛ ዝናብ በእሱ ምክንያት ይከፈታል ተብሎ የታሰበውና ያለቀለት ጦርነት በጣሊዮኖቹ በኩል እንዲተላለፍ ተደርጎአል።

ፍረሃቻ በኢትዮጵያ ወታደሮች ዘንድ በሁዋላ እንዱ እንደጻፈው በፍጹም አይታይም ነበር። የአገር ነጻነት በሞትና በሽረት በደምና በመስዋዕተነት በጀግንነትና በቆራጥነት በሕብረትና በአንድነት ብቻ እንደሚመጣ ከታሪካቸው ከአገኙት የቆየና የነበረ ልምምድና እና ተመክሮ በደንብ አድርገው ያውቃሉ። ይህን የመሰለ ቆራጥ ወኔ ከሌለ ደግሞ ትርፉ የሁዋላ ሁዋላ በሌላው ዓለም እንደታየው ውርደትና ባርነት እንደሆነም በደንብ ያውቁታል።



ለዚህ ነው ተሰባስበው ሁሉም አደዋ ድረስ የወጡት።

ቤተ-ክርስቲያን ለመሳለም ያልሄዱት – ሁሉም ወታደር መንደሩን አለ ትዕዛዝ ጥሎ መውጣት አይፈቀድለትም- ጥዋት ተነስቶ ዛፉን ተደግፎ በየድንኳኑ የተቀመጡትን ከተሸነፉ በሁዋላ ምናልባት ስደተኛ የሚሆኑትን ታቦቶች ከቦ ዳዊቱን ይደግማል ። ድርሳኑን ያነባል። ከአምላኩም ጋር ይነጋገራል።

ሌሎቹ ስለሕልማቸው ከሕልም ፈቺዎች ጋር የዚያን ቀን ጥዋት ላይ ይወያያሉ።ብሩህ ዓለም ፣ትልቅ ዕድል፣ ሐብትና ልጆች አንተን ከዚህ በሁዋላ ይጠብቀኻል። አታስብ ታገኛለህ።ትሾማለህ ፣ትሸለማለህ።አንተ ደግሞ ተጠንቀቅ አለበለዚያ ....ይባባላሉ።

የሚመጣውን የማያውቁ ሴቶቹ ቡና ለቅመው ቡና ቆልተው ቡና በዚያን ሰ▒ት ያፈላሉ። ቆሎ–የቡና ቁርስ- ይቆላሉ። በሶ ያበስላሉ። እንጀራ ይጋግራሉ። እንጨት ፈላጭ፣ በሬ አራጅ ድንኳን ተኳይና አፍራሽ ይንቆራጠጣሉ። ሕጻናት ልጆች ኩብቶች ከበረት ያወጣሉ።በረትም ውስጥ ምን እንደሆን አይታወቅም መልሰው ነድተው ይመልሳሉ።

በአጭር ጊዜ በጥቂት ሰዓታት እስከ አፍንጫው ድረስ ታጥቆ ኢትዮጵያን ቅኝ ግዛቱ ሕዝቡዋንም ባሪያ አድርጎ ለመግዛት የመጣውን የጣሊያን ጦር በወታደሩ ድፍረትና በልጆቹዋ ጀግነኝነት በመሣፍንቱ ሕብረት፣በአንድ ንጉሥ ሥር በመላው ሕዝብ ተሣትፎ በአንዴ ለመደምሰስ ትእዛዝ ብቻ ሳምንቱን በሙሉ እነሱ የሚጠብቁት አሁን ተነስተዋል።

ተነስ የተባለ ሰዓት ያ ሕዝብ እንደ ጎርፍ ነው ያ ሰው ፣ቀፎው እንደ ተነካ ተርብ ሜዳውን ተነስቶ ከንፎ እንደሚያጥለቀልቀው የታወቀ ነው። ትንሽ ቆይተን እንደምናየው የሆነውም ይህ ነው። ሰው ይፎከራል።ቀረርቶ ይሰማል።ሲሮጥ ይወደቃል።ይነሳል።...
ከበሮው፣እምብልታው፣ማሲንቆው፣ነጋሪቱ ...ምኑ ቀረ ይጎሰማል።

ብድግ ብሎ ያ ጦር ያገኘውን ያገኙትን ወደ ሜዳው እየሮጠ ፊቱ ያገኘውን ሰው ሁሉ ፈጀው።


ያየውን የሰማውን አንዱ የጣሊያን ጸሓፊ እንደዚህ አድረጎ ያቺን የቀውጢ ሰዓት ለመጪው ትውልድ አስቀምጦታል።



„… የአበሾች ጦር ወራሪ እንጂ `ጦርነት` አልነበረም።ሕዝቡ ከሁሉም ብሔረሰብ ተወጣጥቶ ቀርቦአል።የሚዋጋው ደግሞ ፈረሱ በቅሎው አህያው ሁሉ በአንድነት ከሰዎች ጋር ተደባልቆ በመሆኑ ግራ ገብቶን ነበር።ጦርነቱን ከወታደሮች ጋር ብቻ አልገጠምንም።

በጦርነቱ ውስጥ ሴቶች ሽማግሌዎች ሕጻናት ቄሶችና ቆማጣዎች ሳይቀሩ ወጉን…“ ብሎ የዚያን ጊዜ በዚያን ዘመን አጃቢ ጋዜጠኛ ሁኖ በጦርነቱ ላይ ጠሳተፈው ካፒቴን ምልቴዶ ከጀኔራሎቹ አፍ ያዳመጠውን ቃል እንደዚህ አድረጎ ጥሩ አድርጎ “በአደዋ ሪፖርቱ ” ላይ ለመጪው ትውልድ እንዲያውቁት ዘግቦአል።

ተአኛ ወገን ይህን የጦር ሜዳ ድልና ትርምስ በጥሩ ቃላት አሳምሮ ያቀረበው ያስቀመጠው/ጡት ፕሮፌሰር አፈወርቅ ገብረ የሱስ ጣሊያን አገር የተማሩ እዚያም ብዙ አመታት የኖሩ ያነበቡ የተመራመሩ ትልቅ ኢትዮጵያዊ ምሁር ናቸው።




በተመሳሳይ ብዕር ከዚያ በማያንስ ለየት ባለ ዓይን ጸሓፊ ትዕዛዝ ገብረ ሥላሴም -አውሮፓ ያልሰነበቱ- በማህደራቸው ላይ አሥፍረውልን ሄደዋል።

አፈወርቅ „…ጦርነቱ ተጀመረ።…ከዚያማ ወዲህ ምን ይነገራል።ኢትዮጵያዊው …አደጋ እንደተጣለበት ባየ ጊዜ የቸኮለው በሌጣው (የቀረው ግን ገና እንቅልፉን አላስብ ተኝቶ ነበር)በሌጣው ፈረሱ ላይ ወጣ። የጣሊያ መድፍ ነው በማለዳ የቀሰቀሰው።…የሸዋ ፈረሰኛ፣የጎጃም እግረኛ የትግሬ ነፍጠኛ ያማራ ስልተኛ ከቦ ያናፋው ይቆላው ያንገደግደው ጀመር።

ከእንዝርት የቀለለ የጁዬ ተኑብር የፈጠነ በገምድሬ ተቋንጣ የደረቀ ትግሬ …(ጠላትን) ፈጀው አሰጣው ዘለሰው።

ወደሁዋላ ቀርቶ የነበረው ሁሉ ነገሩን ሳያውቅ ወደ ዮርነቱ ይጓዝ ነበር።ነገር ግን የጄነራል ባራቲየርን መሸሽና የጦሩነረ መፈታት ባየ ጊዜ ያ ወደሁዋላ የነበረው የታሊያን መድፈኛ መጫኛውን በጎራዴ እየቆረጠ መድፉን እየጣለ በመድፉ ሥፍራ እሱ እየተተካ በአጋሰሱ እየጋለበ ደንግጦ አሥመራ ገባ…“



ጥቂት ቆይቶ እንግዲህ ሜዳው ደም ለብሶ ሣሩ አፈሩ እንዳለ ቀይ ሁኖአል። ጥቁሩም ነጩም ወንድ ልጅ ተናንቆ አደኛው ለባሪያ ፍለጋ ሌላው ለመብቱ- ተያይዘው ወድቀዋል።

ከፍተኛ ጉዳት የደረሰበት ተጋድሞ ያቃስታል።ትንሽ ወይም መጠነኛ ጉዳት የደረሰበት እንደምንም ብሎ አጠገቡ በአገኘው ፈረስ ላይ ወጥቶ እንደገና ጠላቱን አባሮ ለመግጥም ኮርቻው ላይ ለመውጣት ይተናነቃል። ሌላው ጓደኛውን እንዲረዳው ወይም እንዲጨርሰው ከባድ ጥያቄ ያነሳበታል። ሚስቱን ልጆቹን ቤቱንና ሐብቱ እንዳይበተኑ ጧሪ እናትና አባቱ እንዳያጡ ዘመዶቹን ጭምር -ጣሊዩንም ኢትዮጵያዊም – አደራ እያለ ይህን ከአላደረክ ….ውሻ ውለድ እያለ እየረገመ ያንቀላፋል።

በሁዋላ ይህን ጸሓፊ ሁሉ እየቆጠረ እንደጻፈውና እኛ አገላብጠን እንዳየነው ከሁለቱም ወገን በአንዴ እና በአጭር ጊዜ ከ ስንት….ሺህ ወታደሮች በላይ ተረፈረፉ ብለው ደብተራቸው ላይ ዘግበውታል።

በቢላና በሴንጢ በጎራዴና በሳንጃ በጥይተና በመድፍ የቆሰለ ክንድ፣ እንገትና ትከሻ፣ በጥይት የተበተነ ቅልጥም ፣አከርካሪ አጥንት ስንት እንደሆን መገመት ያስቸግራል።

በጣሊያን በኩል አለጥርጥር የቆሰሉትን የሚንከባከቡ ሓኪሞች ነበሩ። በኢትዮጵያ በኩል ከወጌሻ አወቂዎች ሌላ የቆሰለውን ክንድ በጥይት የተመታውን ቅልጥም ማን ቆርጦት ቁስሉን እንደ ጠገነው፣ማን የውጋት ማስታገሻ እንደሰጠ ምንም የምናውቀው ነገር የለም። እኛ የማናውቀው የጦር ሜዳ ቁስል መድረቂያ መድሓኒት፣ውጋት ማስታገሻ፣ጭንቀት ማስረሻ…ቅጠላ ቅጠሎች እና ሥራ ሥሮች ይዘው ይቅረቡ ምንም የምናውቀው ነገር የለም።

ምናልባት የቁራ አራጆች፣የቤተ መንግሥት ወጥ ቤቶች ብልት አውጪ ጎሮምሶች ሐኪም ሁነው የአገራቸውን ልጆች ረድተው እንደሆን እንደዚሁ ምንም የምነውቀው ነገር የለም። ብዙው ጀግና ግን ከአከለ ስንኩልነት ሞትን እንደሚመርጥ አርበኞች – ብዙ ጊዜ አይናገሩም- ከተናገሩ ይህን ውሳኔ እንደሚመርጡ እነሱ ያነሳሉ።

ማታ ላይ ጅብ ወድቆ የሞተውን ወታደር ከሁለቱም ወገን እኩል ቀብሮል።አሞራ የተረፈውን ከእነአጥንቱ አንስቶ ከንሮአል።የተረፈውን በተነጋታው በዚያ በደም በተብከለው ምድር ውስጥ የኢትዮጵያ ወታደሮች ተሰብስበው ቄሶች ፍትሃት አውጥተው፣ጉድጓድ ተምሶ እኩል አንድ ላይ ጥቁሩና ነጩን አንድ ላይ አብረው ቀብረዋል። እነደ አነብብነው የሩሲያ ቀይ መስቀል ሐኪሞች አብረው ተሰልፈዋል። በቁጥር ስንት እንደነበሩ፣ነርሶቹና

አስታማሚዎቹ ምን ይህል እውቀት እንዳላቸው፣የመድሓኒቱ ብዛት ስንት ሳጥን እንደሆነ ምንም የምናውቀው ነገር የለም።

ጦርነቱ ግን በዚሁ ቀን አላለቀም። ሌሎች ተጨማሪ ቀናቶችን ጠይቆአል።

ጸሓፊ ትዕዛዝ ገብረ ሥላሴ አጤ ምኒልክ ለጦርነት የተነሱት እላይ እንደ ተባለው ከገብርኤል ቤተክርስቲያን ሳይሆን ከጦር ሠፈራቸው ነው ይላሉ።



“…በዚያን ቀን የዘቡ ተራ የትግሬው ገዢ የራስ መንገሻ ነበር።500 ነፍጥ የሚሆን የያዙ የሱ ሰዎች ዘብ ሲጠብቁ በየካቲት በ23 ቀን የቅዱስ ጊዮርጊስ ለት ለሊቱን በ11 ሰዓት የኢጣሊያ ወታደር ተሰልጎ መጥቶ ከበሩ ላይ አደጋ ጥሎ ከዘበኛው ጋራ ተታኮሰ። እነዚያም ተታኩሰው ከኢጣሊያኖች 2 ባሻባዙቆችን ማረኳቸው። ምርኮኞቹንም ቢጠይቋቸው እንዲህ አሉ። የአጤ ምኒልክ ሠራዊት ቀለብ ሊመጣ ርቆ ሄድዋል፣ሠፈሩም ባዶ-ነው አደጋ እንጣልበት ብለው ኢጣሊያኖች 4 ጄኔራል ባባ ገሪማ በኩል፣ አንድ ጄኔራል በማሪያም ሸዋቱ በኩል ተሰልፎ መጥቷል ብለው አወሩ።

ይህን ወሬ በሰማ ጊዜ ከዘበኞቹ አንዱ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ሠፈር መሮጥ ጀመረ። ቀኛዝማች ታፈስንም ከመንገድ አገነው።ሌሊቱም አልነጋም፣ገና ጨልሞ ነበርና ማነህ ተባባሉ።ይህነንም ወሬ ነገረው። ቀኛዘዝማች ታፈሰም ይህንን በሰማ ጊዜ ከበቅሎ የነበረውበፈረስ ተዛውሮ ወደ ንጉሡ ድንኳኘ በፈረስ ደረሰ ።የንጉሠ ነገሥቱን የእልፍኝ ዘበኞች ተጣርቶ መምጣቴን ወደ ጃንሆይ አሰሙለeኝ አለ። አጤምነኒልክም ይህን በሰሙ ጊዜ አለጊዜው ስለምንመጣ ብለው ከእልፍኝ ድንኳን ወጥተው ጠየቁት። እሱም ኢጣሊያ አደጋ ሊጥል ተሰልፎ ጠቅሎ መምጣቱን ተናገረ።…” (ከጳውሎስ ኞኞ የተገኘ)

ለሚቀጥሉት ቀናት የኢትዮጵያ ሠራዊት ጣሊያን እያባረረ ከትግራይ አስወጥቶ አሥመራ ድረስ ሸኝቶአቸዋል።

እዚህ ላይ ነው እንግዲህ “የበሰለ የፖለቲካ አካሄድንና እርምጃን የማያውቁ ጥራዝ ነጠቅ ወጣቶች” አንድ የጀርመን የፖለቲካ ሳይንስ ምሁር ጎታ ከተማ በጀርመን አገር ዘንድሮ በተደረገው የመጀመሪያው የምኒልክ ታሪካዊ ጉባዔ ላይ እንዳሉት “ብቅ ብለው …ከመሬት ተነስተው ነገሮችን ሳይመረምሩና ሳያመዛዝኑ አጼ ምኒልክን ኤርትራን ለጣሊያን አሳልፈው ሰጡ የሚባለው ብለው ክስ እሳቸውንም የሚከሱ ሰዎች የያራምዱትና የሚያራምዱት አቋም ተገቢ አመለካከት አይደለም” ብለው የተቹአቻው።



— Avanti, i miei alpini!

መቼ ይህ ብቻ ።

አንድ አዛውንት አርበኛ ተናደው የዛሬ ሃያ አመት ገደማ እንዳሉት- መለስ ብሎ ለማስታወስ የምኒልክ ሐውልት በይፋ በአደባባይ ጩኸትና በጋዜጣ፣ በራዲዮም ጭምር ተለፍፎአል – „ገና”ሰ ውዬው እንዳሉት”… አፍንጫቸውን በደንብ ያልጠረጉ መቀመጫቸውንም ያላበሱ የአገራቸወን ታሪክ የማያውቁ ልጆች የምኒልክ ታላቅነት ረስተው ሐውልታቸው ከአራዳ ጊዮርጊስ ይነሳ፣ ይፍረስ፣የመኮንንም መታሰቢያ ይውደቅ ብለው እሰከመሚገት ድረስ ዘልቀዋል።…ይህን መስማቱ“ ሰውዬው ጭንቅላታቸውን እየነቀነቁ ያኔ እንዳሉት ” ማየቱም መስማቱም … ያሳዝናል ያሳፍራል…“ አርበኛው ብለዋል።

እንደ ምኒልክ በጥቁር ሕዝቦች ታሪክ ውስጥ ገኖ የወጣ የሃያኛው ክፍለ-ዘመን መሪ በአፍሪካ (ማንዴላንና አጼ ኃይለ ሥላሴን አብረው የሚጠቅሱ አሉ) የለም።

እንደእሳቸውም እንደ ምኒልክ በሌላ በኩል „…ተማርን እናውቃለን ከእኛ በላይ ማንም ሰው የለም ብለው በሚመጻደቁ „ሰዎች፣በተለይ ነጻ- አውጭዎች ነን ብለው በሚኩራሩ ሰዎች ዘንድም የተጠላ ንጉሥ“ ( የታወቀውን ክሳቸውን መልሶ ለማስቀመጥ) በአፍሪካ የትም ቦታ የለም።



ምኒልክ በአውሮፓ ነጮች ጣሊያንን መክቶ በማዋረዱ እንደ ተጠላ፣ በዚያውም መጠን ይህን ንጉሥ እንዳከበሩት መጥቀሱ የተጸፈውን መድገም ነው።

ምኒልክ እንደምናውቀው የአገሩን የኢትዮጵያን ነጻነት ብቻ ሳይሆን የጥቁርን ሕዝብ መብት ያስከበረ ጀግና ነው።

ያ ልጅ ሲወለድ ኢትዮጵያ ያኔ በመሣፍንቶች ተከፋፍላ ደክማ ሆና የወደቀች የተረሳች አገር ነበረች። እሱ ብቻ አይደለም።አብዛኛው የዓለም ሕዝብም በጠንካራዎቹ ያኔ ኃያላን መንግሥታት ተብለው በሚጠሩ የአውሮፓ መንግሥታት ሥር፣ በእነሱ በቅኝ ገዢዎች መዳፍ ሥር ወድቃ ፍዳውን ታይ እንደ ዕቃም ትሸጥ ትለወጥም ነበር።

የዛሬዋ ሰሜን አሜሪካ በእንግሊዚና በፈረንሣይ በስፔን ጭምር ተይዛ ትገዛ ነበር። ወረድ ሲባል ደቡብ አሜሪካ በስፔንና በፖርቱጋል መዳፍ ሥር ነበሩ።….እሲያና አውስትራሊያ ደግሞ እንደዚሁ፣በእንግሊዝና በስፔን በሆላንዶች ጭምር ተይዘው ይማቅቁ ነበር።…. ግርክና ቡልጋሪያ መካከለኛው

ምሥራቅና ሰሜን አፍሪካ ደግሞ በተራዋ በቱርክ ሥር ተጠቃለው እነሱ ይተዳደሩም ነበር።

እንደ ምኒልክ በአንዳንድ „ቀባጣሪዎች ዘንድ „ አንዱ እንደ አለው “የተጠላው“ አጼ ቴዎድሮስ ነው። እሱም ንጉሥ ይህን አይቶ ኢትዮጵያን አንድ አድርጎ „ከአውሬዎች አፍ ለማዳን“ የፖለቲካ አካሄዱን በደንብ አላወቀበትም እንጅ ተነስቶ የተቻለውን አበርክቶአል ።

አጼ ቴዎደሮስ ኢትዮጵያን አንድለማድረግ ሲነሱና አባታቸውን ንጉሥ ኃይለመለኮትን አሳደው ድል አድርገው ወጣቱን ምንሊክ እና የሸዋ መኳንንትን ማርከው ይዘው ወደ ጎንደር ሲመለሱ ገና የእናቱንና የአባቱን ፍቅር ያልጨረሰ የአሥር አመት ልጅ -ምኒልክ እንደነበረ ይነገርላቸዋል።

የጣሪክ አጋጣሚ ነው እንጅ- ዕድሜ ለንግሥት ቪክቶሪያ ማለት እንችላልን- ቴዎድርስ ሲሞት እጃቸው የገባችውን ኢትዮጵያን እንግሊዞችም ይዘዋት እሰከ መጨረሻው ሰዓት እስከ 1960 ዓ.ም. (እ.አ.አ) ድረስ – አብዛኛው የጥቁር ሕዝብ አፍሪካ ነጻ የወጣበት ቀን ድረስ እስከዚያ ድረስ እኛንም አባቶቻችንና እናቶቻችን ወንድሞቻችንና እህቶቻችንን ጭምር እኩል ቀጥቅጠው እነሱ በገዙን ነበር።

አንዳንድ ሰዎች አሁን በደርግ ጊዜና ከደርግ ወዲህ በተፈጠረው ሁኔታ ግራ ተጋብተው „የእንግሊዝ ወይም የጣሊያን ወይም የቱርክና የአረቦች…ቅኝ ተገዢ ብንሆን እንሰለጥን ነበር…“ እሰከማለትና እሰከ መመኘት ድረስ ሄደው ይህን ነገር ከአንዴም ሁለቴ እንደ „ጥሩ ነገር“ አንስተው ሲጫወቱ ከሰዎች አንደበት እኔ ብቻ ሳልሆን እናንተም ሳትሰሙት አልቀራችሁም።

ባርነትና የነጮች ተገዢ መሆን ምኑም ላይ ጥሩ ነገር የለውም።እሩቅ ቦታ መሄድ አያስፈልግም። ለአርባ አመታት በተከታታይ የጣሊያን ቅን ግዛት የነበረችው ኤርትራ፣ወይም ጅቡቲ ወይም ሱማሌ ፣ወይም ደግሞ ኮንጎ፣ሊቢያ ግብጽ፣ናይጀሪያ፣ ለሦስት መቶ አመታት በነጮች ሥር የማቀቀቺው ደቡብ አፍሪካ…እነሱ ዛሬ የት ደረሱ ብሎ መጠየቅና መመራመር ተገቢ ነው። በነጮቹ እንደሚባለው ገዢነት የትም አልደረሱም።

ደቡብ አፍሪካና ናይጀሪያ ኬንያና ጋና ለምን የዲሞክራቲክ መንገድን ሲከተሉ ለምን ሱማሌና ኤርትራ እነዚህ እንደላይኞቹ ኮለኒ የነበሩ አገሮች የአምባገነን ሥርዓትን መረጡ? ለሚለው ጥያቄ መልሱን ማግኘት ከባድ አይደለም።

እሱን ግን የተነሳነው ስለምኒልክ ገድልና ሥራ መተረክ ስለሆነ እዚህ ላይ እንተው።

ኢትዮጵያም ነጻነቱዋን ጠብቃ የነጻ- ጥቁሮች መንግሥት ባትሆን ኑሮ፣ አጼ ኃይለ ሥላሴም አይኖሩም ። እሳቸውም በኢትዮጵያ ላይ አይነግሱም። እሳቸው ባይኖሩ ደግሞ ያ የአውሮፓ የቅኝ ገዢዎች መጨፈሪያ አህጉር ሆና የከረመቺው አፍሪካ ፣ በስድሳው አመተ ምህርት በምንም ዓይነት ነጻ መሆኑዋ- በደንብ ከአሰብን- የሚያጠራጥር ነው።

ኢትዮጵያ ባትኖር ኑሮ-ይህ ነው ሓቁ- እንኳን ጥቁር አፍሪካ ጥቁር አሜሪካኖቹም ከነጮች የበላይነት መዳፍ ወጥተው የእኩልነት መብታቸውን ዛሬም -ግልጽ እንሁን- አይቀዳጁም ነበር። ይህን ሓቅ ሌሎቹም አንስተው ተናግረውታል። ደጋግመው ብለውታል።



መቹም ኢትዮጵያን ለመውረር እንደ ቀላል ነገር እንደ መናፈሻ ውስጥ ሽርሽር፣ እንደ ሜዳ ላይ የፈረስ ግልቢያ፣እንደ የወንዝ ወሃ፣ግራና ቀኝ እየመቱ ሲያሸኙም እያንቦጫረቁ እንደመሻገር አድርገው የተመለከቱት ጣሊያኖች ብቻ ነበሩ። ሌሎቹማ ሞክረው አልሆነላቸውም። ምኒልክ ሲታመም እንግሊዞቹም፣ ከእነሱ ጋር ፈረንሣዮቹም፣ጀርመንኖቹም ስንት ተንኮል እንደሰሩ ተጽፎአል።

ምን ያድርጉ አሰብን የመሰለ ወደብ በትንሽ ብር በስምንት ሺህ ማርትሬዛ ቀደም ሰል ከአንዱ የዋህ ነጋዴ ገዝተዋል።ይህ የአሁኑን የመሬት ቅሚያ ወረራ -ሊዚንግን ያስታውሳል።

ምጽዋን አታለው ይዘው በጥቂት ጊዜያት የራስ አሉላን ግዛት ባህረ-ነጋሽን ጨምረው በሁዋላ ያንን አካባቢ ኤርትራ ብላው ሰይመው ፃሊያኖች ባንዲራቸውን ሰቅለው ቁጭ ብለዋል።

ኢትዮጵያን ከያዙ፣ ቀይ ባህርን ከጠቀለሉ፣ሱማሌን ከአካተቱ በሕንድ ውቅያኖስ ላይ የጦር መርከባቸውን ከላይ እስከ ታች ተዘዋውሮና ተንሸራሽሮ አላፊ አግዳሚውን የደም ሥር መንገድ የሚቆጣጠሩበትና የሚያዙበት ቀን እሩቅ እንደማይሆን ለእነሱ ታይቶአቸዋል።

አካባቢው ዱሮም ሆነ አሁንም መንደሩንም ጠረፉንም ባሕሩንም ለመቆጣጠር አመች እንደሆነ ለሮማውያኖች ገና ዱሮ ግልጽ ነበር። ጥንታው ግሪኮችም ከቱርክና ከአረቦችም ጋር ሁነው ይህን ያውቃሉ።ቀይ ባህርን የያዘ የእሲያና የአውሮፓን መገናኛ በር ያዘ ማለት ነው።

ከዚያም በላይ-ብዙዎቹ እንደሚገምቱት፣ በከርሰ መሬቱ ውስጥ ነዳጅ ዘይትና ጋዝ አለው።እዚያ ባህር ውስጥ ግሩም ጣት የሚያስቆረጥሙ የባህር ፍራ ፍሬዎችና የማይጠገቡ የዓሣ ዓይነቶችና ዘሮች ብዙም ሳይደከምበት የሚጠመድበት፣የሚሰበሰብበት ቦታ ነው።

ከባህሩ ወጣ ሲሉ ግሩም አየር ያለው የኢትዮጵያ ደጋው አካባቢ ያ ምድር በተፈጥሮው የሚማርክ ነው። አለፍ ሲሉና ወረድ ሲሉ ደግሞ መሬቱ ለስንዴና ለገብስ ለቦቆሎና ለጥራጥሬ ለሥጋ ከብትና ለዶሮ እርባታም መሓል አገሩም በሕዝብ ብዛት ለተጣበበቸው የጣሊያን ዘር ጥሩ መሰፈሪያና መኖሪያም ያመቸ ነው። ርቀቱም ከሮም እሩቅ አይደለም። በመርከብ በቀላሉ ይደረስበታል።

እንደሌላው የአፍሪካ ግዛቶች ደጋውና ወይነ ደጋው የኢትዮጵያ መሬት አውሬና ወባ ወይም ተላላፊና አስፈሪ በሽታዎች የሉትም። ቀዝቀዝ ያለው አየሩ ይህ ደግሞ የትም በትሮፒካል አፍሪካ የማይገኝ ቦታና ምድር ነው።

እንግዲህ በጥጋብና በንቀት -ነጭ በመሆናቸው ብቻ -በማንቋሸሽና በመጥላላት -ትንሽ በመቅላታቸው ብቻ – በጭንቅላት ጨዋታ እኛ እንበልጣቸዋለን በሚለው የዘረኝነት አመለካከት- የእኛን የቆየ ጥበብና ብልሃት ባለማወቅ- ኢትዮጵያን በዚያውም በቀላሉ የምሥራቅ አፍሪካን አካባቢ ከሌሎቹ ቀድመን እኛ እያዛለን በሚለው ከንቱ ምኞታቸው በኢትዮጵያ ላይ ጣሊያኖቹ የድብቅ ጦርነት አውጀው አምባላጌ ላይ ቀደም ሲል ገብተው እዚያ መሽገዋል።

በትክክል ለመናገር ጦሩ በኢትዮጵያ ላይ የታወጀው አድዋ ላይ አይደለም። ጦሩ የታወጀው ከእንግሊዝ መንግሥት ጋር ተስማምተው ምጽዋን የያዙ ዕለት ነው።

ኢትዮጵያን ለመያዝ ደግሞ ሥነ-ልቦናችንን እና ባህሪአችንን አስተሳሰባችንና አካሄዳችንን በደንብ ጊዜ ወስደው እነሱ አጥንተዋል።

ትንሽ እነሱ ያስቸገራቸው፣ያስቸግሩ ይሆናል ብለው ያሰቡት እነሱ እራሳቸው„ሸዋ“ ብለው ነጥለው የሚጠሩት „የአማራው“ ሕዝብ ክፍል ነበር።

እንደ አንድ ሰው ሆኖ የተነሳባቸው ግን ወደሁዋላ ላይ ቆየት ብለን እንደምናየው „አማረው“ ብቻ ሳይሆን ሁሉም -መቁጠር አያስፈልግም- ድፍን የኢትዮጳያ ሕዝብ ነው። ይህን ማስተባበር ደግሞ አንድ ምሁር እንደአለው የምንልክ ችሎታ ነው።

ትግሬና አማራ፣ጎንደሬና ጎጃሜ ወሎና ሐማሴን፣ኦሮሞና ከፋ፣ እስላምና ክርስቲያን፣ካቶሊክና ኦርተዶክስ፣ሱማሌና አፋር፣ደቡብና ሰሜን....አንዳንዶቹ ችግሮች ብቻ ለመጥቀስ፣ በዘር በቋንቋ፣ በዘውዱ ይገባኛል ጥያቄ ፣በእበልጥ ፉክክር፣በንቀት በቅናት... ነጮቹ ተዘዋውረው በአካሄዱት ጥናቶች እንደደረሱበት „አለመግባባት“ (በሕዝቡ መካከል አይደለም) በገዢው መደብ ተወካዮች መካከል እንዳለ ተገንዝበዋል።

ዘውዱ ምኒልክ እጅ ያኔ በመግባቱ ሌላው የገዢ ክፍል አኩርፎአል። ሌላው ቀርቶ የዮሓንስ ዘውድ በኑዛዜው መሰረት ለራስ መንገሻ በመሰጠቱ የትግራይና የሐማሴን መሣፍንት ራስ መንገሻን ከድተው እጃቸውንም ግዛታቸውንም ይዘው ለጣሊያን ማስረከቡን መርጠዋል።

ደጃች ባህታ ሐጎስ አካለጉዛዬን፣ደጃች ደብብ አሥመራንና አካባቢዋን ፣ባላምበራስ ክፍለ ኢየሱስ ደግሞ ከረንና ቦጎስን እንደ ገጸ-በረከት ጋዜጠኛው ጳውሎስ ኞኞ እንደ ጻፈው እንደ ገጸ-በረከት ለጣሊያን መንግሥት ማበረከቱን እነሱ መርጠዋል።

ጄኔራል ባራቲየሪ የጣሊያን ጦር ዋና አዛዥ ይህን ተመልክቶ ሌሎችንም ግንዝቤዎች ከግምቱ ውስጥ አስገብቶ ፣ ኢትዮጵያን ወሮ ነጻነቱዋን ገፎ ያንን እሱ እንደአለው „ንጉሠ ነገሥት ነኝ የሚለውን ምኒልክ የሚባለውን ሰው ከብረት በተሠራ ቅርጫት እንደ ዱር አውሬ እጅና እግሩን አሥሮ በሮም መንገድ ላይ ለተሰበሰበው ሕዝብ የምሥራቹን እየጎተተኩ አቀርባለሁ...“ብሎ እሰከ መፎከር ድረስ ይህ ሰው እንደሄደም መገንዘብ ይቻላል።



ምኒልክን በብረት ቅርጫት በቀፎ ውስጥ የተመኘ ሰው -ያውም ደግሞ በሮም መንገድ ላይ በሰንሰለት ለመጎተት እቅድ ያወጣ ሰው- ለሌቹ ተራው ሕዝብና ለመሣፍንቶቹ ምን እንደተመኘ መገመት አያስቸግርም።እንግዲህ ምኒልክ ይህን አይቶ ነው ይህንንም ሰምቶ ነው ግሩም የሆነውን ፖለቲካውን የቀየሰው።

የዱሮውን የሮም ኢምፓየር ግርማ ሞገስ ለማስመለስ አርፍዳ የተነሳችው ጣሊያን እንደ ኢትዮጵያ ያለች „ትንሽ“ ጭዳ አገር እንደምንም ብላ ፈልጋ አግኝታለች። ይህንን የይገባኛል ፍላጎት ቀደም ሲል በርሊን ላይ በተካሄደው አፍሪካን የመቀራመጥ ጉባዔ ላይም አንስታለች።

ሮም -ጥንታዊት ሮም- ያኔ በአውሮፓና በሌላው ዓለም በምትፈራበትና በምትከበርበት ዘመንና ጊዜ ድል የመታቻቸውን አገር መሪዎች በብረት ሰንሰለት አሥራ በሮም መንገድ ላይ እንደ ጥሎሽ ትጎትታቸው እንደነበር መጽሓፍም ላይ በላይብረሪ በፊልም ቤት ጊዜ ያለው ሰው ይህን ነገር ሊመለከት ሊከታተል ይችላል።

በዘመናቸው ሮማውያን ፈረንሣይንና እንግሊዝን ጀርመንና ግሪክን ...ስላቭንና ባልካንን ባሪያ እድርገው መንገድ ላይ ነድተው አዋርደው እነሹ ገዝተዋል።

ያንን ነበር እንደገና እነሱ ከአንድ ሺህ ስንት መቶ አመት በሁዋላ ተመልሰው ተቋቁመው -በገዛ ድካማቸው ተከፋፍለው ተበታትነው የወደቁት- ለዓለም ሕዝብ እንደገና ለማሳየት የፈለጉት።

ሮም ሁሉን አዋርዳ የእርሻ መሬቱን ቀምታ ወርሳ፣ ከብቶቹን እየናዳች ህዝቦቹዋን ስትቀልብ ያኔ እላይ የተጠቀሱት አገሮች የዛሬን አያድርገው ዝም ብለው ያዩዋት ነበር።

ከሁለት ሺህ አመት በሁዋላ „ሥልጣኔና ትምህርትን፣ ባርነትንና ድህነትን ከኢትዮጵያ አጠፋለሁ „ (በዚህ መፈክር ነው ሌሎቹ የአፍሪካ ግዛቶች የተያዙት በእንደዚህ ዓይነቱ ጥሪ ነው አሁንም አንድ አገር የሚወረረው ...) ይህን ለኢትዮጵያ አመጣለሁ ብላ በአለፈው ክፍለ-ዘመን ጣሊያን ወደ ኢትዮጵያ የመጣችው። ይህንንም “የሮም ሥልጣኔ አዋጅ” ሕዝቡ አጨብጭቦ እንዳይቀበል እንቅፋት የሆነውን ንጉሥ „በብረት ቅርጫት አሥሬ ማን እንደሆንኩ አሳያለሁ „ የሚለውም ዛቻ – የዶሮውን የሮም በላይነትን በተዘዋዋሪ ለአውሮፓያኖች ዞር ብለው እንዲያስታውሱት- በተዘዋዋሪ መልዕክቱን እንዲያዳምጡት የተደረገው።

ምኒልክንና ጣይቱን መኮንንና ጎበናን፣ገበየሁንና መንገሻን፣ዳርጌንና ወሌን አሉላንና ባልቻ አባ ነፍሶን እና...(ጀግኖቹ ቆጥሮ መጨረስ አይቻልም) በብረት ቀፎ ወደ ሮማ አሥሮ ለመውሰድ የተመኙት የጣሊያን ጄኔራሎች በአንድ ቀን በተካሄደው ጦርነት አድዋ ላይ እነሱም ከነሕልማቸው ጭምር ተንኮታኩተው እንዲወድቁ የተደረገው።

ያ ምኒልክን በብረት ሰንሰለት ያለው ጄኔራልም ወታደሮቹን ሜዳ ላይ በትኖ የራሱን



ነፍስ ለማዳን ሸሽቶ አሥመራ ገብቶአል።ይህ ሰው ሸሽ ተብሎም የሁዋላ ሁዋላ የጦር ፍርድ ቤት ቀርቦ ፍርዱን የተቀበለው።

የምኒልክ ጉዞ በተለያዩ እቅጣጫዎች እነዚህ ሁሉ ፈጠራ ሳይሆኑ – የታሪክ ጸሓፊዎች ተስማምተው እንደሚሉት- በደንብ የተመዘገበ ታሪክ ነው። እነዴት እነደነበር ብሎ መለስ ብሎ መመልከቱም ለማንም ሰው ጠቃሚ ነው።

አንደኛው እሰከ አሁን ድረሰ በብዙ ጻሓፊዎች ዘንድ ትልቅ አተኩሮ ያልተሰጠው የምኒልክ እና የምኒልክ አማካሪዎች በዚያን ዘመን -ይህን በደንብ አላምጦ መዋጥ ያስፈልጋል- ለፕሬስ የሰጡትን ትልቅ ሚና እንደገና መመልከት ጠቃሚ ስለሆነ ጥሩ ነው።




ስለመጀመሪያው የኢትዮጵያ ጋዜጣ ስለ አእምሮ ምስረታ እይደለም አሁን ወደ መጨረሻው ላይ የምናነሳው። ከዚያም በፊት ስለነበሩት በብራናና እና በበሬ ግንባር ላይ ስለ ሚጻፉት፣እነሱንም ስለሚመዘግቡት ጸሓፊ ትዕዛዞችና ካህናት ጉዳይ እነሱም ስለ ነበራቸው „የአመለካከት ነጻነትና አቀራረባቸው ስልት“ አይደለም አሁን ወደመጨረሻው ላይ ለማንሳት የተፈለገው።

የንጉሠ-ነገሥቱን የጦር ሠፈር ስንመለከተው (ስለ ጣሊያኖቹ መንደር ሌላ ጊዜ እናነሳለን) ምኒልክ „እኔ ብቻ አውቃለሁ እናንተ ግን ዝም ብላችሁ እርፋችሁ ትዕዛዜን ተቀበሉ“ የሚሉ መሪ እንዳልነበሩ አንረዳለን።

ሰውዬው „ምክርን“ የሚመርጡ ለምክር ትልቅ ቦታ የሚሰጡ ብዙ ከመናገር የሰውን ሓሳብ የሚያደምጡ፣አዳዲስ ሓሳቦችን የሚያስተናግዱ የሚያመዛዝኑና ከዚያም በተገኘው አዲስ አመላካከትና አስተሳሰብ ከዚያ ተነስተው „ፍርድ“ መስጠትን የሚያስቀድሙ ናቸው። የሚያስቸኩል የሚያንቀዠቅዥ ነገር ስለሌም እንደገና አሰላስሎ ለመመልከት ነገርን ማሳደር የሚመርጡም መሪ ናቸው።

በአንድ በኩል ይህ ነው ችሎታቸው የአገሪቱን መሣፍንትና መኳንንቶች፣የጦር አለቆችንና ካህናትን ሰፊ ዕውቀት ያላቸውን የአገሪቱን ሊቃውንቶችንና ሊቀ-ሊቃውንቶችን፣ወይዛዝራትና የቤት እመቤቶች ሳይቀሩ ፣ወይ በቡድን ወይም ደግሞ ተራ በተራ በነፍስ ወከፍ እየጠሩ የሚሰነዘሩትን ሓሳቦች እያዳመጡ መላ የሚመቱት ጥሩ ንጉሥ አድርጎአቸዋል።



በሌላ በኩል ከፈረንሣይና ከሩሲያ ከአርመንና ከግሪክ ከጀርመንና ከኦስተሪያ -ከሲዊስ የመጡ መልእክተኞች ይሁኑ፣ ነጋዴ መንገደኞች ወይም ተቀጥረው የሚሰሩ አማካሪዎችን እየጋበዙ የእነሱንም አመለካከት የሚያዳምጡ ሰው ወጥቶአቸዋል።ሌላው ቀርቶ ከእራሳቸው ከጣሊያኖቹ ጋርም እሰከ መጨረሻው ሰዓት ድረስ ይነጋገሩ ነበር።

አዚያው ላይ እያወቁ መሣፍንቱንና መኳንንቱን በእሳቸው ላይ ለማሸፈት በድብቅ ከራሶችና ደጃዝማቾቻቸው ጋር የሚገናኙትን ባለ-ሙያዎቻቸውን „...እስቲ ጣሊያኖቹ ምን እንደሚሉ አዳምጡአቸው“ ይሉም ነበር።

“ለመኮንን ምኒልክን ከኩዱ ሐረርን በንጉሥነት፣ለሚካኤል ወሎን ለዳርጌ ሸዋን ለተክለ ሃይማኖት ሰሜንና በጌምደርን ለመንገሻ ደግሞ የንጉሠ-ነገሥት ዘውዱን እንሰጣችሁዋለን...” ብለው እንደሸነገሉአቸው እንደሚሸነግሉአቸው ምኒልክ እያውቁ “በርቱ አዳምጡ ይሉአቸው” ነበር።

ቢጨንቃቸው ጣሊያኖቹ አንድ ቀን ወጣቱን የአውሮፓ ተማሪ የራስ ዳርጌን ልጅ ፣ልጅ ጉግሣን ከትምህርት ቤት ጠልፈው እሱን ለማንገሥ ወደ አደዋ አምጥተው ጦሩን ለመበተን የማይሆን ሙከራ አድርገዋል። ይህንንም የምኒልክ የጦር ሠፈር በደንብ ያውቀዋል።

የምኒልክ ችሎት አስቦበት (ነገር እናሳጥር) ጣሊያን ከምሽጉ አውጥቶ አውላላ ሜዳ ላይ ለመምታትና ለመቅጣት ሁለት ምሥጢር የያዙ “መሰረተ ቢስ ወሬዎችን” በጥንቃቄ የጣሊያን ጆሮዎች እንዲገቡ አድርገዋል።

አንደኛው ንጉሥ ምኒልክ ከአገራቸው ከወጡ በሁዋላ በረጅሙ አድካሚ ጉዞ በየዱሩና በየገደሉ መንከራተታቸው “በጠና ክፉኛ ታመዋል። ራስ ወሌም ሳይታሰብ በድንገት ሞተው ከዚህች ዓለም ሕይወታቸው አልፎአል” የሚል ሲሆን “ወታደሩም የኢትዮጵያ ዘማች ጦር” -ያኔ በያለበት ስንቅና ቀለብ በጎተራ የትም አልተቀመጠም- “የሚበላው አጥቶ ረሃብ ገርፎት ለዝርፊያ በሁሉም አቅጣጫ ወጥቶ ተበትናአል። ስለዚህ ጊዜው አሁን ነው..” የሚለው አጓጊ ዜና ይጨመርበታል።

በአናቱ „ክረምቱ ሳይገባ ወንዙ ሳይሞላ ወደቤታቸውና ወደግዛታቸው መመለስ የሚፈልጉ መሣፍንቶች ምኒልክን ጥለው ከድል አድራጊው ከሮማ መንግሥት ጋር አብረው ለመቆምና አብረው የበላይነቱን ተቀብለው ለመሥራት ስለአሰቡ ጦርነቱን እባካችሁ ቶሎ ክፈቱና ገላግሉን እኛም ዞር ብለን ከእናንተ ጋር ተደባልቀን የምንልክን ጦር ብዙ ደም ሳይፈስ ከውስጥ ሆነን እናንተ እየገፋችሁ ስትመጡ እንበትነዋለን....“ የሚል “ዕውነተኛ ” መልዕክት የያዙ ሁለት መልእክተኞች በስውር ወደ ጣሊያን ምሽግ (በመሣፍንቱ ስም) በመላክ ” አዲሱን ሤራ ፍላጎታቸውን ” ይገልጹላቸዋል።

ሦስት ቀን በመሉ በረሃብ ተጠብሶ አንዲት ጠባቂ የሌላት ትንሽ ጠቦት በግ እንዳገኘ ጅብ የጦሩ አዣዥ ጄኔራል ባራቲየር ዘሎ የዚህን ወሬ ቀንድ ይነክስና ለወራት የመሸገበትን ካምፕ ጥሎ ወደ አደዋ ሜዳ ይወርዳል።

“ሤራው ” ይሰራል። እዚያም አንዱ እንዳለው „...አፈር ድሜውን” እሱ ለጥቂት እግሬ



አውጭኝ ብሎ ሲያመልጥ „እሱ የሚመራው ጦር ይበላል።“

ይህ ዜናም ዓለምን በአንዴ ያዳርሳል።

በጣሊያኖች ጥበብና በእነሱ በንቀት ላይ በተመሰረተው ብልሃትና ዘዴ ይህ -በድል አድራጊው በጥቁር አፍሪካ ጦር የመመታታቸው ዜና- ዓለምን በምንም ዓይነት አያዳርስም ብለው እነሱ ገምተው ነበር።

ግን ለዚህ-ይህ ነው የመዝጊያችን ነጥብ- ኢትዮጵያኖች አውጥተው አውርደው እነሱም እንደ አቅማቸው ደግሰው የሚከተለውን መልስ አዘጋጅተው ጠብቀው ነበር።

እሱም በዘመናዊ አነጋገር የሓሳብና የሥነ ልቦና ጦር የሚባለውን ስም ያተረፈው መንገድ ነበር።

ስለዚህ ነገር በሰፊው ተጠቅሶ ባለመጻፉ አሁን ይህን ነገር ለመጀመሪያ ጊዜ የሚያከታተሉ ሰዎች አዲስ ይመስላቸዋል እንጂ ጋዜጠኛው ጳውሎስ ኞኞ እግዚአብሔር ነፍሱን ይማረውና በዘመኑ ተናዶ አንስቶታል።

ለማስታወስ።

የአደዋን ዘመቻ ለማክሸፍ አጤ ምኒልክ ሦስት አብይ እርምጃዎችን የሁዋላ ሁዋላ የማይቀር ነገር ነው ብለው – ይህም ለአገሪቱም ለኢትዮጵያ፣ ለእሳቸውም በታሪክ ፊት የሚጠየቁበት ስለሆነ መጪውን ሁኔታም ተረድተው፣(ወጣ ወረደ ለማንም ሰው ቢሆን የመኖርና የአለመኖር ጥያቄም ስለሆነ -ምናልባትም ነገሥታቱ ሲነግሱና ቅባ ቅዱሱን ተቀብተው ዘውዱን ሲደፉ በጆሮአቸው ካህናቶቹ አንድ ነገር ተናግረዋቸው ሊሆን ይችላል… ምን ይታወቃል ?- ወይም የፖለቲካ ችሎታ ?… ሌላ ጊዜ ግን በእርግጥ በዚህ ጉዳይ ላይ እንመለስበታለን ) እሳቸው „ አጤ ምኒልክ እምዬ ምኒልክ“ ወስደዋል።

አንደኛው -ይህ ነው ምኒልክን ከቴዎድሮስም ሆነ ከዮሐንስም የሚለያቸው አንድ ነጥብ- „በይገባኛል ጥያቄ በየአለበት የሚበጣበጡትን መሣፍንቶች አንድ ሳላደርግና እነሱን ሳላሰባስብ ጦርነት ማንም ይምጣ ማን ከፍቼ ላሸንፍ አልችልም „ ብለው በማሰባቸውና ለዚያም መፍትሔ በመፈለጋቸው ነው።

ለዚህም ነው ፣በእርግጥም በምኒልክ የግዛት ዘመን በእሳቸው ሥር „….ጦር አንስቶ የተዋጋቸውንም አንከባክበው ቁስሉንም አክመው አብረው በልተውና ጠጥተው ሾመው ሸልመው…ግዛቱን ወይ ለእሱ ወይም ለልጁ ሰጥተው…እንደ ልማዱና ባህሉ እንደ ወጉና ሥርዓቱ እንዲያስተዳድር ግን ደግሞ መልሶ ከድቶ ከሌላው ጋር ቆሞ እንዲነግጦ እንዳይወጋቸው አስጠንቅቀው“ ከሁሉም ጋር ተከባብረውና ተቻችለው ኑረዋል።

በዚህም ብልሃት የውጭ ጠላትን ተንኮል አክሽፈው መያዣና መጨበጫ አሳጥተዋል።

ሁለተኛው የምኒልክ ብልሃት እንደ ሚቀጥለው እንደዚህ ነው። ሌላው የአውሮፓ ኃያላን መንግሥታት ከጣሊያን ተሻርኮ በቡድን ወይም በነጠላ እንዳይወጋቸው ከጦርነቱ በፊት ሳይሆን ከጦርነቱ በሁዋላም „የጣሊያን ምርኮኞችን ሲከባከቡ፣የሞቱትን ሲቀብሩ፣ወደ አገራቸው ለመመለስ የሚፈልጉትን ወይም ከዘመዶቻቸው ጋር በደብዳቤ ለመገናኘት የሚፈልጉትን….እኔ ይህንና ያንን ለማድረግ ዝግጁ ነኝ ….“እያሉ ለተለያዩ የአውሮፓ መንግሥታትን ለቫቲካን ጳጳሳት ጭምር የሚጽፉትን ደብዳቤ ዛሬ ስንመለከተው በዲፕሎማቲክ የአሰራር ዘዴ ንጉሡ የሚጫወቱትን ጨዋታ -ይህ ደግሞ ብልጣብልጥነት ሳይሆን ከልብ የመነጨ የፖለቲካ እርምጃ (መቶ አመት ይበልጠዋል)ይህን መመልከቱ በጣም እጅግ በጣም የሚደነቅ ነው።

ሦስተኛው እኛን አሁን በነጻ የኢንፎርሜሽን ልውውጥ ዘመን ያደግነውና ያሳለፍነውን ትውልድ የሚገርምና የሚያስደንቅ የአባቶቻችን ሥራ ነው።

ምንድነው ያደረጉት?

ጦር ሜዳ የሆነውን ነገር፣…የተገኘውን ድል፣…ከጣሊያን ጄኖራሎች ጋር በፍጥጫው ጊዜና ሰዓት የተደረገውን ንግግር ሳይቀር፣…. ድክመታቸውንና ጥንካሬአቸውን፣…ሽሽታቸውንና ውድቀታቸውን፣ስለተማረኩት ወታደሮች፣ስለ መሣሪያ ክምችታቸውና ስንቱ በእጃቸው ላይ እንደወደቁ ሳይቀር አንድ በአንድና፣ተራ በተራ እራሳቸው አጼ ምኒልክ እና ግራዝማች ዮሴፍ በሌላ ሰው ስም በዚያ መልክ እየጻፉ ወደ አዲስ አበባ እየላኩ (ይህ ነው ችሎታቸው) እዚያ የሚገኙትን የውጭ አገር ዲፕሎማቶችንና ተወካዮችን በጦር ሜዳ ከዚያ በተገኘ ዜና በየጊዜው እነሱን ይመግቡአቸው ነበር። „… ፊውዳል ፊውዳል ምንም የማያውቁ መሓይም ፊውዳል … የሚለው ቀባጣሪ ዛሬ ይህን ሲሰማ „ አንዱ ወዳጄ እንዳለው „ እንደተለመደው የአማራ ፈጠራ ነው ሊል ይችላል።“ ግን አይደለም። ዕውነቱ እንደሚቀጥለው ነው።

እነሱም ይህን የመሰለ ዜና የሚደርሳቸው የዓለም መንግሥታት አምባሳደሮች በተለይ የፈረንሣዩና የሩሲያው ተጠሪዎችና ዲፕሎማቶች፣ የደብዳቤውን ይዘት እየገለበጡ፣እያጣፈጡና እያሳመሩ፣ወደ ፓሪስና ወደ ሞስኮ ወደ ለንደንና ወደ ጣሊያን ጭምር ለጋዜጣ አሳታሚዎች ይልኩ ነበር።


በዚህ ነው ጣሊያኖች እዚያ „….እየተለበለቡና እየተቀጡ፣ጦር ሜዳ ላይ ድል እየተመቱና እየሸሹ….አሸነፍን፣እያሸነፍን ነው…ድሉ ዞሮ ዞሮ የእኛ ነው „ የሚለውን የሐሰት ወሬ በአገራቸውና በአውሮፓ ሲያናፍሱት ፣ኢትዮጵያኖች -ይህን ማን ያላሰበውን ጨዋታ እነሱ በየጊዜው በሚልኩት ዜና እየተከታተሉ ያኔ ያጋልጡት፣ያጋልጡትም የነበረው።

ይህ ነው እንግዲህ እኛን ዛሬ ቁጭ ብለን ያለፈውን ታሪክ የምንከታተለውና የምናየውን ሰዎች በመጨረሻው „…እነዚያ ምንም የማያውቁት -በነጮቹ ፕሮፓጋንዳ የተባሉት ገና መገራትና ሥልጣኔ የሚባለውን ነገር ከክርስትና ሃይማኖት ጋር ከእሱም ጭምር መማር አለባቸው የተባሉት አሕዛብና አውሬ ኢትዮጵያኖች – …“ በዘመናቸው የሰሩት ሥራ።

ምኒልክና አባቶቻችንና እናቶቻችን ጭምር አንድ ላይ ሁነው ኢትዮጵያን አመቻችተው ለሚቀጥለው ትውልድ አስተላፈዋል። ሌላው ቀርቶ የምኒልክ ሞት ኢትዮጵያን ለመያዝ ለአሰፈሰፉት ኃያላን መንግሥታት በር ይከፈታል ብለው አባቶቻችን ያንን ሰዓትና ጊዜ ለእኛ እና ለአገሪቱ

ደህንነት ሲሉ ደብቀዋል።

ምኒልክ አዲስ አስተዳደርን፣ ዘመናዊ ትምህርትን፣ጥበብና ዕውቀትን፣ሕክምናና ቴክኒክን፣በተለይ ከቅኝ ግዛት እኛን አድነው ወደ ሃያኛው ክፍለ ዘመን አስገብተዋል።



እርግጥ ኤርትራን በነበረው የሚሊተርና የጊዜው ችግር -ረሃብ ነበር፣ክረምት ገብቶ ነበር፣ሁሉንም ማጣት ነበር- ንጉሡ ምኒልክ ያን አካባቢ ለማስመለስ አልቻሉም ነበር።

ኤርትራ ግን አቶ ዘውዴ ረታ እንደ ጻፉት በአጼ ኃይለ ሥላሴ ብርታት በኢትዮጵያ ዲፕሎማቶች ጥረት፣በዓለም አቀፉ ውሳኔ ተመልሳ ከእናት አገሩዋ ከኢትዮጵያ ጋር እንደገና "ተዋህዳለች።" ተመልሳም ይህች አገር የዛሬ ...አመት ተገንጥላለች።ተገንጥላም የአንድ ሰው አምባገነን መዳፍ ውስጥ- በዚህ ላይ ስምምነት አለ – ይህቺ አገር ገብታለች። „....ነጻነት ወይስ ባርነት"-ጥያቄው ያኔም አሁንም እንዳለ ነው።

ዳግማዊ ምኒልክ „ባርንትን አጥፍቶ እኛን ከነጮች ባርነት አድኖናል።"

ጊዜው አሁን ከዚያ „ከየሃያኛው ክፍለ-ዘመን መጨረሻ ዑበደት" በሁዋላ „የሣልሳዊ ምኒልክ ጊዜ ነው።"

እሱ ደግሞ „ዘውድ የደፋ ቅባ ቅዱሱን የተቀባ የአንድ ንጉሥ ኢትዮጵያ ወይም የአንድ ድርጅት ኢትዮጵያ ..." ሳይሆን ለተወሰነ ጊዜ ብቻ እንዲያስተዳድር በሕዝብ የተመረጠ፣ ተቀባይነት ያለው አስተዳደር ማለት ነው። „ሣልሳዊ ምንልክ" ደግሞ ፣እንሰብሰብውና ሓሳባችንን ሸብ አድርገን እንዝጋው፣ ... አንተም እሱም፣እሱዋም፤ያቺም- ሕዝብ ከመረጣችሁ ያውላችሁ መንገዱ- ማንም የኢትዮጵያ ዜጋ ለአጭር ጊዜ ኃላፊነቱን የሚቀበልበት ጊዜና ዘመን ማለት ነው ።

አቶ አሰፋ ጨቦ አንድ ጊዜ ተገርመው የዛሬ ሃያ ወይም ሃያ ሁለት አመት ገደማ አገራቸውን ጥለው ወደ አሜሪካን አገር ሳይገቡ ቦን ከተማ ላይ አንድ ነገር እኚህ ሰው ....አማራ፣ ትግሬ፣ ኦሮሞ፣አፋር፣ጉራጌ፣ሱማሌ፣ኤርትራ፣ኩናማ...ነፍጠኛ የሚባለው ፌሊጥ ያኔ በዚያ የኢትዮጵያን ሕዝብ በዚህ መከፋፈል ጌጥ በነበረበት ዘመን...ሰውዬው እነደዚህ ብለው ነበር።

„.... ምኒልክ በገጽተው" አቶ አሰፋ ጨቦ "... እኔን ይመስላል! ነፍጠኛ! ነፍጠኛ አማራ ...አገር ለቆ ይውጣ... የሚለውን ቃል አልቀበለውም " ብለው ሓሳባቸውን ሰንዝረው ነበር።

ዕውነትም ምኒልክ ሁላችንንም ኢትዮጵያኖችን – ትርጉሙም ጥቁር ማለት ነው- ጥቁር ሕዝቦችን በሙሉ ይመስላል።ይወክላል።ለእነሱም ሙብት መከበር በተግባር ተዋግቶአል።

በ ዘሥራ ዘጠነኛውና በሃያኛው ክፍለ-ዘመን በሰላም አልጋው ላይ የአረፉ የኢትዮጵያ ንጉሥ ማን ነው ቢባል ምኒልክ ብቻ ነው።

ምን ይታወቃል በሰላማዊ ምርጫ ዘመን ፣ እኛም አንድ ቀን አራትና አምስት ጠቅላይ ሚኒስትሮቻችንን ከእነ ፕሬዚዳንቶቻችን (የክልል አይደለም) አብረን አቁመን አሰልፍን አንድ ቀን -እንደ አሜሪካና እንደ ጀርመን እንደ እንግሊዝና ፈረንሣይ እኛም እነጋብዛቸው ይሆናአል። እዚያ ላይ ለመድረስ ግን የብርሃን ፍልስፍናን ኢንላይትሜንትን አኻኮ መዋጥ ያስፈልጋል።

ይልማ ኃይለ ሚካኤል

ለአእምሮ የህዳር **2006/ November/December 2013** እትም **/ –** ዳግማዊ ምኒልክ **–** ቅጽ **2**፣ ቁጥር **4/**

About these ads